አንጋረ ፈላስፋ
(የፈላስፎች አነጋገር)

ከሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ (ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተተረጎመ)
ጥቅምት 23፤ 1953 ዓ/ም (ለግርማዊነታቸው 30ኛ ዘመነ ንግሥ መታሰቢያ)

ቅኝት፤ መስፍን ማሞ ተሰማ

በህወሃት/ኢህአዴግ 25ኛ ዘመነ አገዛዝ በወርሃ ግንቦት 2008 ዓ/ም (ሜይ 2016) ተፃፈ፤ ሲድኒ አውስትራሊያ

"ይህ ቅኝት በኢትዮጵያ ወህኒ ቤቶች በግፍ ለሚማቅቁት የሕሊና እስረኞች ሁሉ መታሰቢያ ይሁን!"

{ፈላስፋ በወህኒ ቤት በራፍ ላይ እንዲህ የሚል ፅሁፍ አነበብኩ አለ፤ ይህች ቦታ የመከራና የጭንቅ ናት፤ ያልሞቱ (በሕይወት ያሉ) ሰዎች የሚቀበሩባት መቃብርም ናት። የወዳጆች መፈተኛ፤ የጠላቶች መደሰቻ የሆነች ቦታ ናትና።} አንጋረ ፈላስፋ

ማስታወሻ፤

አንድ፤ ከ"ፍሬ ሊቃውንት" መፅሀፍ በማህበረ ቅዱሳን 1999 ዓ/ም - በቃኘው አጥሮ የቀረበ።

ይህ ሞገስ ነው ትሉኝ ይሆናል። ግን እኔ ምሳሌው /ሥዕሉ/ እንጂ ሞገስ አይደለሁም። ሞገስ አንድ ነው። እኔ የሞገስ ሥዕል ግን አንድም ብዙም ነኝ። ሞገስ ከአንድ ቦታና ከአንድ ቤት ይገኛል። እኔ ግን /ሥዕሉ/ ከብዙ ቦታና ከብዙ ቤት እገኛለሁ። ሞገስ ዛሬ አለ። ነገ ግን እንጃ። ከነገ ወዲያ ግን በእርግጥ የለም። እኔ ሥዕል ግን ዓለም እስካለ ድረስ ከእናንተ ከህያዋን ጋር አለሁ። ይሁን እንጂ እሱ ሲታመም የማይታመም፤ እሱ ሲሞት የማይሞት አንድ ነገር በአደራ ሰጥቶኛል። ይኸውም በሶስት ቀለሞች የቆመ ስም ነው። እስካሁን ድረስ ከእኔ አልለየውም።

ይህንን ምርምራዊ ሃይለ ቃል የተናገሩት ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ናቸው። የሃይማኖት፤ የፍልስፍና፤ የምርምር መፅሀፍ ደራሲው ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ በኤርትራ ክፍለ ሃገር በሀማሴን አውራጃ መስከረም 1 ቀን 1907 ዓ/ም ተወለዱ። ከ 12 ዓመታቸው ጀምሮ በትምህርት ሲታነፁ፤ በሊቃውንት ሲገነቡ ኖሩ። በትግራይ፤ በጎንደር፤ በአዲስ አበባ።

ሊቀመዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ሞገስ አስገዶምና አብረሃ ደቦጭ በግራዚያኒ (የፋሽስት ኢጣሊያ የጦር ጀኔራል) ላይ ቦንብ ወርውረው ጉዳት ባደረሱበት ጊዜ ከአርበኝነትና ከስደት የተረፈው የአዲስ አበባ ህዝብ በፋስ፤ በአካፋ፤ በመጥረቢያ ሲጨፈጨፍ፤ ቤት ተዘግቶበት በእሳት ሲጋይ የዐይን ምሥክር ነበሩ። ሌሊቱን በሙሉ በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን እያደሩ የሀገራቸውን ነፃነት መመለስ ተግተው በፀሎት ሲጠይቁ፤ ተይዘው በአስቸጋሪ ሁኔታም ውስጥ ታስረው፤ አልፈዋል። ነፃነት እስኪመለስ ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት በማስተማር ሀገርና ቤተ ክርስቲያን የጣሉባቸውን አደራ ተወጥተዋል።

ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ዘጠኝ የተለያዩ መፃህትን አዘጋጅተው ለትውልድ አበርክተዋል። መፃህፍቶቻቸው ከይዘታቸውና ከመልዕክቶቻቸው ጋር **የኢትዮጵያ መለያ የሆነውን የፊደልና የፅሁፍ ባህል ተጠብቆ እንዲቆይና እንዳይበረዝ የሚያስገነዝቡ ናቸው፤** (ለምሳሌ "የህፃናት አንደበት መፍቻ") የሚለው መፅሀፋቸው። ካሳተሙዋቸው መካከል በ1962 ዓ/ም ያወጡት የአማርኛ መዝገበ ቃላት አንዱ ተጠቃሽ ነው። ያልታተሙ ግና በምዕመናን እጅ የሚገኙ ሰባት መፃህፍትም አሏቸው።

ሊቀ መዘምራን ሞገስ፤ **"ኢትዮጵያ ጥገኛ በመሆን የፊደልና የሥነ ፅሁፍ ተመፅዋች አለመሆን፤ የራሷ ፊደልና ሥነ ፅሁፍ ያላት ሀገር ስለሆነች ቋንቋውን በየጊዜው እያሻሻለች የነበረችና የምትኖር ታሪክና የታሪክ መዝገብ የሆነች ሀገር ናት"** በማለት ይህ ሁሉ በቤተ ክርስቲያኗ ብርታትና ታታሪነት የተገኘ መሆኑን ያወሳሉ።

ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ በአስመራ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር አባል ሆነው በየካቲት 1978 ዓ/ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተደረገው የደራሲያን ማህበር ጉባኤ ላይ ተሳትፈዋል። ስብሰባውን

አጠናቅቀው ወደ አስመራ እንደተመለሱ ለጥቂት ቀናት ታመው በተወለዱ በ71 ዓመታቸው በ1978ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

ቤተ ክርስቲያን በየዘመናቱ በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊ ዕውቀት የበለፀጉና የደረጁ አባቶች ነበሯት። አሁንም ኣሏት። ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ከእነዚህ ስመ ጥር አባቶች መካከል አንዱ ነበሩ። አሁን በአካለ ሥጋ ቢለዩም የአእምሯቸው ውጤት የሆኑት ሥራዎቻቸው ግዘፍ ነስተው ዘመን ተሻግረው ዛሬም ወደፊትም እንዲታወሱ ያደርጋቸዋል። "ስም ከመቃብር በላይ" ይሏል እንዲህ ነው። (ሙሉው ታሪክ ከላይ ባጣቀስነው መፅሀፍ ውስጥ አለልህ)

ሁለት (ከቃኚው)

በዛሬዋ ኢትዮጵያ በሰፈነው የከፋ ዘመን ቀበሌያዊ ወረርሽኝና ጎጣዊ ልክፍት ሊቁን ሊቀመዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስን እንኳን ባይችሉ ከሥራዎቹ መካከል "አንጋረ ፈላስፋ"ን ቀበሌያዊ/ወንዛዊ ቀለም የሚቀቡት ይኖሩ ይሆናል። አንባቢ አስቀድመህ ይህንን ልብ በል፤ **አንጋረ ፈላስፋ በቀዳሚነት የማንም ሳይሆን የፈላስፎች ሕሊና ውጤት ሲሆን ይህንንም ጠብቃ ያኖረች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ናት።** "አንጋረ ፈላስፋ" ከሌሎች ቋንቋዎች ወደ **ኢትዮጵያ ቋንቋ ግዕዝ** ዘመኑ እጅግ በራቀ ዘመን **በኢትዮጵያውያን** ተተረጎመ። ግርማዊ ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ኢትዮጵያን በሚያስተዳድሩበት ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ ከግዕዝ ወደ አማርኛ በቤተክህነቱ ሊቅ ሊቀመዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ተተረጎመ። **ሊቁ ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ከህልፈቱ በፊት ለ60 ዓመት የኖረባትን ኢትዮጵያ በዛሬው አይንህ አትመልከታት፤ ያኔ የዛሬውን አልነበረችምና!** ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ በእናት ሀገሩ ኢትዮጵያ የሚያምንና የሚመካ ኩሩ ኢትዮጵያዊ የኤርትራ ተወላጅ ስለመሆኑም አስቀድሞ ያቀረብንልህ ታሪኩ ማስረገጫ ይሁንህ። እኛም ሊቁንና መፅሀፉን የቃኘንበት ዐውደ መንፈስ በዚያው በጥንቱ ሊቁ በኖረባትና በሚያምንባት ኢትዮጵያ ዘመነ መንፈስ መሆኑንም አስተውል። . . . ማስታወሻችን አበቃ።

አስቀድመን ይህንን እንጠቅሳለን፤

"የናንተ ሙያ የሚታወቀው አሁን አይደለም። ጊዜና ትውልድ ካለፈ በሁዋላ ሥራችሁና ሥማችሁ እንደገና በአዲስ መልክ ቀርቦ ታሪክ ሲያስታውሰው ነው። የፅሁፍም ፍሬ የሚለቀመው ካፈራ በሁዋላ ስለሆነ የናንተም የሥራ ፍሬ የሚታወቀው ካለፋችሁ በሁዋላ ነው።

"ይህንን እናንተ የፃፋችሁትን ማስታወሻ ይዞ የሚመጣው ትውልድ ዕውነተኛውን ታሪክ ለመፃፍ ሲጠቀምበት ነው። መጪው ትውልድ ይህንን የናንተን የሥራ ፍሬ መነሻ በማድረግ በበለጠ ድልና ዕድል ለማግኘት መንገዱ ተከፍቶለታል።" ***ግርማዊ ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ*** *(አንጋረ ፈላስፋ)*

<u>መንደርደሪያ</u>

አንጋረ ፈላስፋ የፈላስፎች አነጋገር ነው ይለናል ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ። ሊቀ መዘምራንን ስለምን በአንቱታ አልጠራነውም? በቃኚው ግንዛቤና ዕምነት ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ - ሊቀመዘምራን - የነፍስም የስጋም መምህር የሆነ፤ የፈላስፎችን ምሥጢረ ጥበብ ያነከተ፤ ፈላስፋ ነበር እንኳን ባይባል ደቀመዝሙራቸው የነበረ ወይም ነፍሱ ለፈላስፎች የቀረበ፤ ለዚህም ሥራው ዋቢ የቆመ፤ ነውና እንደፈላስፎቹ ከአንቱታው ይልቅ አንተ ይስማማዋልና፤ ይህም ለርሱ ያለንን ክብር መግለጫችን ይሆናልና - የሚል ይሆናል መልሳችን።

"ይህ አንጋረ ፈላስፋ የተባለው መፅሀፍ ከክርስቶስ ልደት በፊት በየዘመናቸው የተነሱ የግሪክ (የሌሎችም አገር) ፈላስፋዎችና እንዲሁም ከክርስቶስ ልደት በሁዋላ የተነሱ መንፈሳውያን ሊቃውንት ከተናገሩዋቸው ምርጥ ምርጥ ቃላት ተውጣጥቶ ***በቀድሞዎቹ የኢትዮጵያ ሊቃውንት*** *ትጋት የፅርዑን ከፅርዑ' የዓረብኛውን ከዓረብኛ ቋንቋዎች ወደ ግዕዝ የተገለበጠ ነው።" ይላል በመቅድሙ ሊቀመዘምራን ሲያስተዋውቀን።*

ምን? ቀደምት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ወደ ግዕዝ የተረጎሙት? የግሪኮቹን ከላቲን የመካከለኛው ምሥራቆቹን ከአረብኛ? ድንቅ እንጂ ታሪክ!

የቀደምቶች ታሪክ ቢሉ፤ ሰንበት ባለው ሰሞን አንጋፋው ምሁር (ጥንታዊውን ከዘመናዊው ትምህርት ያቀናጁት) ፕሮፌሰር ጌታቸው ሀይሌ እንዲሁ ከግዕዝ (አሁን ዘመን የጥበብ መግለጫ ቋንቋው ግዕዝ ብቻ ይመስለኝ ጀምሯል። እዚህ ላይ አንባቢ ሆይ አስተውል! የጥበብ መጀመሪያው አላልኩም። የጥበብ መጀመሪያው እግዚአብሄርን መፍራት ነውና) "ሀተታ ዘዘርዓ ያዕቆብ" እና "የአባ ባሕርይ ድርሰቶች" በሚሉ ርዕሳን ከግዕዝ ወደ አማርኛ የመለሷቸውን ክቡድና ብርቅ ሥራዎች አንብቤና ውስጤ ተነክቶ በእኛና

በቀደሙት ኢትዮጵያውያን መካከል ዘርፈ ብዙ ጥያቄዎችን እያነሳሁ ስምሰለሰል - አልተው ያለኝ ልማዴ - “አንጋረ ፈላስፋ”ን ጨመረልኝ። እሰይ! እንኳንም ጨመረልኝ፤ የተውኩትን ቅኝት ስላስነሳኝ።

እና እንግዲህ የዚህ ዘመን ወጣት ትውልድ ሆይ ይህንን ልብ በል! ቀደምቶችህ ሊቃውንት ነበሩ። ሀይማኖተኞች ነበሩ። ይቅር ባይ ነበሩ። ፈላስፎች ነበሩ። አፍቅሮተ ህዝብ ያደረባቸው ነበሩ። ለሀገራቸው ቀናዒ ነበሩ። ለባንዲራቸው ሟች ነበሩ። ታሪክ ሰሪ ነበሩ። በዛሬው አንተነትህ ውስጥ ቀደምቶቹ አሉ። እና አቅርባቸው እንጂ አትካዳቸው፤ አክብራቸው እንጂ አትወርፋቸው፤ አርማቸው እንጂ አታጥፋቸው፤ በጎ ምግባራቸው ላይ ቀጥልባቸው እንጂ አታውድማቸው፤ ዘክራቸው እንጂ አታንኳጣቻው። ቀደምቶችህን በማዋረድ፤ ታሪካቸውን በመካድ፤ ሥራቸውን በማውደም፤ ስማቸውን በመበከል አንዳች የምትጠቀመው የለም። የምታዋርደው ራስህን፤ የምትክደው ራስህን፤ የምታወድመው ራስህን፤ የምታጠፋውም ራስህን ነውና! እና . . . ይህንን በአንክሮ እልሃለሁ፤ እኔ በትውልዴ ያጠፋሁትን አንተ አትድገመው - ዘወትር ይፀፀተኛልና!

እንግዲህ ወደ ቀደመ ጉዳያችን እንመለስ፤ ሊቀመዘምራን ሞገስ ይቀጥላል-

“. . . ከፈላስፎች አንዱ ‘ጊዜ፤ ዕድሜ፤ ቦታ፤ ፈቃድ፤ ችሎታና ስምምነት እነዚህ 6ቱ ነገሮች ከተረዳዱ ሥራ ሁሉ ይፈፀማል’ እንዳለ ሥራንና አሰሪን ከጊዜ ጋር ለማገናኘት የተለየ ችሎታ ገንዘቡ የሆነ መልዕልተ ባህርይ እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ሌሎች ዓለማት ከደረሱበት የሥልጣኔ ደረጃ ለማድረስ የተቀደሰ ፈቃዱ ስለሆነ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴን አስነስቶ ከ1914 ዓ/ም ጀምሮ በኢትዮጵያ የሚገኙ መፃህፍት ከግዕዝ ወደ አማርኛና ወደተፈለገው ቋንቋ እየተተረጎመ በዘመናዊ አታሚ መኪና በብዛት እየታተሙ ለገዳማቱ፤ ለአድባራቱና ለህዝብ ሁሉ እንዲደርሱ አደረጉ።” ይለል ሊቁ ተርጓሚ።

አዎ፤ ሀቅ ነው። የግርማዊነታቸውና የዘመነ መንግሥታቸው ሌጋሲ ከሆኑት ቋጥኝ ሥራዎች መካከል አቢይ የሆነው ትውልድን በትምህርት የማነፅ ወደር የማይገኝለት አባታዊ ትጋታቸውና ለትውልዱ ያጎናፀፈውም ውጤት ነው።

ይሁንና ከደርግ እስከ ኢህአዴግ (ኢሠፓ፤ ኢሕአፓ፤ መኢሶን፤ ህወሃት፤ ኦነግ፤ ሻዕቢያ) መሥራችና አመራር ሰጪ የሆነው በንጉሡ መንግሥት የተማረው ያ ትውልድ (የተጠቀሱት አንጋፋዎቹና ሌሎቹም ድርጅቶች እንደ ትውልድ በ ያ ትውልድ ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸውና) ግርማዊነታቸውንና መንግሥታቸውን በአመፅ አውርዶና በጭካኔ ለግብዐተ መሬት አብቅቶ ያመጣው ለውጥ ቢኖር፤ በሀገር ሉዐላዊነት ቢሉ በህዝቦች መስተፋቅርና አንድነት፤ በትምህርት ጥራትና ብቃት ቢሉ በሀገር አስተዳደርና ሥነ ምግባር፤ በሀገር በታሪክ በባንዲራ ፍቅር ቢሉ በዜግነት ኩራት፤ እነሆ ላለፉት አራት አሥርታት የቁልቁለት ጉዞውን በየዘርፉ ተያይዞት ይገኛል።

ያ ትውልድ ዛሬ ዘመን ድረስ (ከአርባ ዓመት በሁዋላም) ከወደቀበት ይቅር ተባብሎና ተደጋግፎ እንደመነሳት ከሞት የተረፈውም እርስ በርሱ እሳትና ጭድ እየሆነ ድርጅት በድርጅት ላይ መፈልፈሉ ሳያንስ፤ ለአራት አስርታት የቀጠለው ሥራውና መዘዙ ቀጣዩን ትውልድም በየዘርፉ መመረዙ ይባስ።

ሊቀ መዘምራን ሞገስ የግርማዊነታቸውን ሠናይ ምግባር ፅፎ ቆሰቆሰንና አስፃፈን እንጂ እኛስ እንደ ያ ትውልድ አባልነታችን ያኔ - **ሳናውቅ በድንቁርና** ለምሳሌ ‘ያልተገራ ፈረስ ጠቅል እያላችሁ/ ከማይጨው ፈርጥጦ ለንደን ገባላችሁ’ እያልን በአደባባይ ስንዘምር - ታሪክንና ትውልድን (ቀደምቶቹን) ለማዋረድ ሆን ተብሎ የተፈበረከ ፍፁም ሀሰት የሆነ ታሪክ መዘመራችንን መች አውቀነው? ይሁንና እንዲህ ያለውን የታሪክ ክህደት ሆን ብለው የፈጠሩት ከያኔው የተማሪው መሪዎች መካከል ካልሆነ ከየት ሊሆን ይችላል? (ያ ትውልድ የጀመረው የታሪክ ፍብረካው መዘዝ አሁን ዘመን ድረስ ዘልቆ እየተራቀቀና እየተወሳሰበ ቀጥሏል)። **አውቀን በድፍረት** ለምሳሌ፤ ህፃናትን፤ እናቶችን አባቶችን፤ አረጋውያንን፤ እርጉዞችን፤ ዐይነ ሥውራንን፤ . . . ሠላማዊ ህዝብ የጫነን አንበሳ አውቶቡስ መንገድ ላይ አድፍጦ - በግርማዊነታቸው መንግሥት ላይ የተቃውሞ ሠልፍ በማድረግ ስም - በድንጋይ እሩምታ መስታወቶቹን ማድቀቅ፤ ተሳፋሪውን ሠላማዊውን ሕዝብ ደመ ከልብ ማድረግ - መሆኑን መች ልብ ብለነው? እግዚኦ መኻረነ! ለመሆኑ ስንቱን ህዝብ ይሆን ለስንት መከራ የዳረግነው? . . . እና ዛሬ አረጋዊ ዕድሜያችን ላይ ሆነን ያኔ በግንፍል ወጣትነት (በማወቅም ሆነ ባለማወቅ) ላጠፋነው ሁሉ ይቅር ባይ አምላክ ይቅር እንዲለን ከመፀለይ ያለፈ አቅም የለንምና ይህን እዚህ ላይ ከድነን ወደ ቀደመ ጉዳያችን እንዝለቅ።

ለመሆኑ አንጋረ ፈላስፋን መተርጎም ለምን አስፈለገ? ብንል ሊቀ መዘምራን እንዲህ ይመልሳል፤ “አንጋረ ፈላስፋ የተባለ መፅሀፍ በአንዳንዱ ታላላቅ ገዳማትና አድባራት ካልሆነ በቀሩት አብያተ ክርስቲያናት ስለማይገኝ ተጠቃሚዎቹ አንዳንድ ተመለልካቾች ነበሩ እንጂ ብዙዎች አልነበሩምና . . . መላው ህዝብ

በተለይም የጊዜው ወጣቶች አስተማሪዎችና ተማሪዎች እንዲካፈሉትና እንዲጠቀሙበት በማሰብ ከግዕዝ ወደ አማርኛ መተርጎሙ የተሻለ መስሎ ታየኝ" - ይላል ተርጓሚው ሊቅ።

ስለ ትውልዱ ብቻ ሳይሆን ስለ ተተኪው ትውልድም የሚጨነቅ የነበረው ከያ ትውልድ በፊት የነበረው ትውልድ አካል የሆነው ሊቀመዘምራን ሞገስ የዘመኑ ተማሪዎችና አስተማሪዎች የሥራውን በረከት ይቋደሱ ዘንድ፤ ተቋድሰውም ከጥበበኞቹ ፈላስፎች የኑሮ፤ የአስተዳደር፤ የአስተሳሰብ የወዘተርፈ የህይወት መንገድ ጠቋሚ ትምህርት ፈልቅቀው እንዲያገኙ በማሰብ መተርጎሙን ሲነግረን - ሀገራዊ አክብሮታችንን ስንቸረው ሥራውም ዘመን ተሻጋሪ፤ ትውልድ አስተማሪ መሆኑን እኛ ደግሞ በዘመናችን አንብበን ብንመሰክር ቢያንስበት እንጂ ቢበዛበት አይደለም። እንቀጥል ምልከታችንን፤

"ስተረጉመው ምንም እንኳን አነጋገሩ አጭር ሆኖ ምሥጢሩ የረቀቀና የጠለቀ ቢሆን የተቻለውን ያህል ከዘይቤው በጣም ሳይርቅ መሰረታዊ ሃሳቡን ሳይለቅ አንዳንድ ጊዜም ሀይለ ቃሉንና ምሥጢሩን ለማፍታታት መግለጫውን እየሰጠሁና አስተያየቴንም እየጨመርሁ ነው።

"በዚያውም ላይ ሥነ ፅሁፉ ከሠለሞንና ከሲራክ መፃህፍት ጋር እንዲሁም ከሐዲስና ከብሉያት መፃህፍት አልፎ አልፎ ስለሚገናኝና ስለሚመሳሰል መሰል መሰሉን እንደ ጥቅስ አድርጌ አግብቼበታለሁ። ከጥንታዊ አባቶች ሲያያዙ የመጡትን ምሳሌዎችና ተረቶች አንዳንድ በህይወተ ሥጋ የሚገኙ ታላላቅ ሰዎችም የተናገሩዋቸው ምርጥ ቃላት ከሚመሳሰሉዋቸው ቃላት ጋር እንዲዛመዱ አድርጌያለሁ።" ይላል ሊቀ መዘምራን።

ሊቁ ያነበበ፤ አንብቦም የመረመረ፤ መርምሮም ያገናዘበ፤ አገናዝቦም የሩቁን ከቅርቡ የዘንድሮን ከድሮ አዋህዶ የተረጎመ፤ ትውልድን ያስተሳሰረ አባቶቹን ያከበረ፤ ምሳሌያቸውን የገበረ የዘከረ ሆኖ እናገኘዋለን። የመፅሀፉ ይዘት መንፈሳዊና ጥበበ ሥጋዊ መሆኑንም ይናገራል። አያይዞም ሊቁ ሲያፍታታ፤

"ይህን መፅሀፍ መላልሰው የሚያነቡና የሚመለከቱ ሰዎች ልቡናቸው በዕውቀት እንዲራቀቅ ከማድረጉም በላይ በምሥጢር የረዘመ፤ በንባብ የተከረከመ አጭሩን አነጋገር በቀላሉ እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል። በተለይም የዘመኑን ወጣቶች አስተማሪዎችንና ተማሪዎችን ከሐይማኖት እንዳይርቁ በዕውቀት እንዲራቀቁ ከሚያደርጋቸውም በላይ የዛሬ ጊዜ ሳይንቲስቶች ዕውቀታቸውን እስከዚህ ድረስ ለማስፋፋት የቻሉት የነዚህን ፈላስፎች ፍልስፍና መነሻና መሪ በማድረግ እንደሆን ከዚያው ሊያገኙት ይችላሉ።

". . . መፅሀፉን የሚመለከት ሰው ሁሉ የየራሱንና የሰዎችን መጥፎም ሆነ መልካም ጠባይ ከዚያው ያገኘውና **ተፈጥሮው ከሰብዐዊ መስመሩ ወጥቶ ወደ አራዊት ጠባይ ያዘነበለበት ካልሆነ** ሀኪሞች በብዙ ድካም ሊያድኑት ካልቻሉት ከመጥፎ ጠባዩ ሳይድን (ሳይታረም) አይቀርም ተብሎ ተስፋ ቢደረግበት በዕውነቱ ቃለ አጋኖ መስሎ ሊታይ ባልተገባ. . .

"የተፃፈው ሁሉ እኛን ለመምከርና ለመገሰፅ ተፃፈ። በትዕግስታችንና መፃህፍትን በመመልከት ተስፋችንን እናገኝ ዘንድ. . ." (ሮሜ 15፤4)

እነሆ ሊቀ መዘምራን የፈላስፎችን ምሥጢረ ጥበብና የታላቁን መፅሀፍ ቃል አስማምቶ "የተፃፈው ሁሉ እኛን ለመምከርና ለመገሰፅ ተፃፈ" በሚል አስሮታል። ይልቁንም ደግሞ ገራሚና ጠሊቅ ቃል ሆኖ ለቃኘው የታየው "ይህን መፅሀፍ በማንበብ ተፈጥሮው ከሰብዐዊ መስመር ወጥቶ ወደ አራዊት ጠባይ ያዘነበለበት ካልሆነ . . ." በሚል ያቀረበው ራዕይ አዘል ምልከታው ነው። ለማንኛውም በቅኝታችን እየጠለቅን ስንዋኝ አስቀድሞ ሊቀ መዘምራን ያነሳውን ነቁጥ በምንቀነጭባቸው (መቼም ቅኝት ነውና) መልዕክቶች ልናፍታታው እንጥራለን። አንባቢ ብቻ በርታ፤ አንባቢ ብቻ በርቺ . . .

ተርጓሚው ፈላስፋ ሊቀ መዘምራን መፅሀፉን በሁለት ክፍሎች (ከክርስቶስ ልደት በፊት በኖሩ ፈላስፎችና ከክርስቶስ ልደት ወዲህ በሀዲስ ኪዳን ዘመን በነበሩት መምህራን) ትምህሮች ላይ ያዋቀረው ሲሆን በሃያ ዘጠኝ ምዕራፎች ከፋፍሎት በ180 ገፆች ተጠቃሏል። በሁለት ቅጂ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ከላቲንና ከዐረብኛ ወደ ግዕዝ የተረጎሙት አንጋረ ፈላስፋ የተገኘውም በአቡነ እንድርያስ ገዳም እና በደብረ ቢዘን ገዳም መሆኑን ገልፆ ትርጉሙን ያስኬደው ሁለቱን በማስተያየት እንደሆንም ፅፏል። ቃኚው ለአቅርቦት ያመቸው ዘንዳ የተለያዩ "ራስ ወለድ" ንዑስ ርዕሶችን እየከፈተ በኒያ ሥር ዝምድና ያላቸውን እያዛመደና እያዋደደ ዕይታውን ያወርዳል። (በዚህ ቅኝት በሁለተኛ የሰዋስው መደብ - አንተ/አንቺ -<ለምሳሌ ተመልከት፤ አስተውል ወዘተ> መጠቀማችን የሊቁን አፃፃፍ ስልት መከተላችን መሆኑን አስተውል)። ደግሞም ሊቀመዘምራን ማለት ትርጉሙ የመዘምራን አለቃ ማለት መሆኑን ልንጠቅስ እንወዳለን።

<u>መልዕክተ ሊቀ መዘምራን</u>

እነሆ በዚህ ርዕስ ሥር ጥቂት አንቀፆችን በቁማቸው (ያለ ማብራሪያ) እናወርዳለንና ተቀበል።

"በዚህች መፅሀፍ ውስጥ ብዙ ያማረ ያማረ የምክርና የእዝናት ነገርና እንደጨው የጣፈጠ በጎ በጎ ነገር ይገኛል። ለሚጓዝባት ሁሉ ጎዳናነቷ የቀና ነው። ልብ ብሎ ለሚሰማትም ተሰሚነቷ ቀላል ነው። . . . ይኸውም የፈላስፎች ፍልስፍናና ዕውቀት ነው። ከብር ከወርቅ ከአልማዝ እርሷ ትበልጣለች ትመረጣለችም። (ምሳሌ 15፤16) . . .

"ዕድሜህን ሙሉ ብትማር ከፈላስፎች አንደበት በመስማት ልታውቀው የማይቻልህን አርፈህና ቀስ ብለህ ይህችን መፅሀፍ ካነበብህና ከተመለከትህ ባንድ ወር ውስጥ ታውቀዋለህ። ረብህ ጥቅም በሚገኝበት በር ታቆምሃለች። . . . የምትችለውን እንጂ የማትችለውን እንድታደርግ አታስገድድህም። የምትችለውን እንጂ የማትችለውን ትሸከም ዘንድ አትገፋፋህም። የምትችሉትን እንጂ የማትችሉትን መከራ አግኝቷችሁ ትጠፉ ዘንድ ያልተዋችሁ እግዚአብሄር ምሥጉን ነው። (1 ቆሮ፤10፤13)

"በስህተት መጠራጠርንና ክፉ ማድረግን ካንተ ታርቃለች። አንደበትህ እንዳይዘላብድ ታቃናዋለች። . . . መፃህፍት የጥበብና የአዕምሮ መዝገብ ናቸው። አዕምሮም የነፍስ መኖሪያ ቦታ ናት። ነፍስም የማስተዋል ሃይል ናት። ሰው ሁሉ ክብር ሥጋዊንና ክብር መንፈሳዊውን የሚያገኘው በአዕምሮና በጥበብ ነው። . . . ከሰነፍ ሽማግሌ ብልህና አስተዋይ ወጣት ይሻላል። ጥበብና ተግሳፅ ተርታውን ሰው ታላላቅ ሰዎች ከደረሱበት ደረጃ ያደርሱታል። ከትልቅ የተወለደንና ከተርታ ሰው የተወለደውን ሳይለያዩ ያከብራሉ፤ ያስከብራሉ።

(ከትልቅ ወይም ከትንሽ መወለድ ሙያ አይደለም። ራስን ለትልቅ ክብር መውለድ ግን ሙያ ነው) ግርማዊ ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ።

እነሆ ይህ እንግዲህ ሊቁ ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ስለ መፅሀፉ ፋይዳ ከራሱ የዕውቀት ባህር እየጨለፈ ከታላቁ ቅዱስ መፅሀፍ እያዋደደ፤ ከታላላቅ ሀገሀራዊ ሰዎች ምክር እያጣቀሰ በስፋት ካወረደልህ ላይ የቀነጨብነው ነው። ይህን ማድረጋችን ስለምን ይሆን? አንጋረ ፈላስፋን ፈልገህ አፈላልገህ ለማንበብ እንደ ውሃ ጥም በፍላጎት ትቃጠል ዘንዳ ፈልገን። ይህም ክፉ አስበንልህ አለመሆኑን ታውቃለህና። ወይም ልቡናህ ይነግርሃልና።

አሁን ደግሞ የሊቁን መልዕክት በራሱ አንደበት ቋጭተን ወደ ፈላስፎቹ አገር እንገባለን። ". . . ከእንግዲህ ወዲህ ግን በመፅሀፉ ውስጥ ያሉትን ፈላስፎች ስም ስማቸውን እየጠራ ያሉትን እገሌ ፈላስፋ እንዲህ አለ፤ የሌሉትን አንድ ፈላስፋ እንዲህ አለ እያለ ይፅፋል።"

እናመሰግናለን ሊቀ መዘምራን። ከዚህ በሁዋላ ያለውን ተርጉመህ፤ ተንትነህ፤ አዛምደህ ያቀረብክልንን - እኛ ደግሞ እንደዘመናችን፤ እንዳቅማችንና እንደ ዕይታችን - ምሥጢሩን ለማወቅ፤ አውቀን ለማዛመድ፤ አዛምደንም ዛሬን ለመመዘን ነገን ለመመልከት እንጥርበታለን።

<u>ሀገር እና መሪ</u>

"አርስጣጣሊስ እስክንድርን ሲመክረው እንዲህ አለው። ዓለም ገነት (የአትክልት ቦታ) ናት፤ በአትክልት ቦታ ትመሰላለች። አጥሯ ቅጥሯም ንጉሥ ነው። ንጉሥም ሠራዊት የሚያጅቡት፤ መኳንንት የሚከቡት የህዝብ እረኛ ነው። ሠራዊትም ለገንዘብ የሚገዙ፤ ለጦርነት የሚታዘዙ ናቸው። ገንዘብ ከመንጋዎች (ህዝብ) የሚሰበሰብ ሀብት ነው። መንጋዎችም ቅንነት የሚገዛቸው ባሮች ናቸው። ቅንነት ግን ልማድ ናት። እሷም ለዓለም ጤናና ፀጥታ ነች።

"ቅን ፍርድ የዓለም ሃይል ፅንዕ፤ የበጎ ሥራዎች ሁሉ መሰረት ናት። ገንዘብ የሚበዛው፤ አገር የሚለማው፤ ህዝብ የሚበለፅገው ቅን ፍርድ በመፍረድ ነው። ፍትህ (ቅን ፍርድ) ህዝብንና ህዝብን ያፋቅራል፤ ህዝብንና መንግሥትን ያስማማል። ዓለም ፀንቶ የሚኖረው ቅን ፍርድ በመፍረድ ነው።' {አለ}

አንባቢ ሆይ፤ ምልከታችንን ከማስፈራችን አስቀድሞ የሚከተለውን እናወርዳለን - ለግንዛቤ።

እንግዲህ አርስጣጣሊስ በማለት ቀደምቶቹ የኢትዮጵያ ሊቃውንት የተረጎሙት የግሪኩን ፈላስፋ አሪስቶትልን ነው። እሱም የተወለደው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ384 ዓመተ ዓለም ሲሆን የሞተው ደግሞ በ322 ዓ/ዓለም ነው። እስክንድር ተብሎ የተተረጎመውም ታላቁ ንጉሥ አሌክሳንደር በመባል የሚታወቀው

ግሪካዊ ንጉሥ ሲሆን የኖረውም ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ356 እስከ 323 ዓመተ ዓለም ነው።. . .አሁን ምልከታችን ይከተላል።

እነሆ ከክርስቶስ ልደት በሁዋላ በሀገረ ኢትዮጵያ አቆጣጠር 2008 ዓመተ ምህረት፤ በምዕራቡ 2016 በተጋመሰበትና ኢትዮጵያም በህወሃት/ኢህአዴግ ዘመነ ግዛት ሩብ ምዕተ ዓመት (25 ዓመት) ባስቆጠረችበት በያዝነው ዘመነ ዮሐንስ ወርሃ ግንቦት ላይ ሆነህ አርስጣጣሊስ ለንጉሥ እስከንድር የለገሰውን ምክርና (እስከ ቅኝታችን ማከተሚያ የሚነቀሱትን ሌሎችንም ጨምሮ) የምታነብ ኢትዮጵያዊ ሆይ! . . . ለዛሬ ከማንኛውም አካል ወገንተኝነት ገለል በልና፤ ሀገርህንና ህዝብህን ብቻ ወገን አድርገህ፤ በኢትዮጵያ ሠማይ ላይ የተዘረጋውን አገዛዝ ቀደምት አባቶችህ ሊቃውንት ከተረጎሙልህ የፈላስፎቹ ትምህርት እያነፀርክ ተመልከት። እኛ እምናቀርበው የአንጋረ ፈላስፋን ምልከታችንን/ቅኝታችንን ብቻ ነው። አመዛዝኖ፤ አስተያይቶ መፍረዱ ያንተ ህሊና ፈንታ ይሆናልና . . .ይኸው ጀምረናል።

አርስጣጣሊስ በጥቂት መስመሮች ነገር ግን በአያሌ አንቀፅች/ገፆች ሊተነተኑ የሚችሉ የአንድን ሀገር መንግሥት ተግባርና ሃላፊነት ከክርስቶስ ልደት በፊት ለኖረው የሀገሩ ንጉሥ (መሪ) መከረ። እነሆ መንግሥትህ የምትፀናው ህዝብህን በቅንነት ስታስተዳድረው ነው። ቅን ፍርድ የበጎ ሥራዎች ሁሉ መሠረት ናትና አለው። በጎ ሥራ ምንድን ነው? በጎ ስራ ስለ ህዝብ ስለ ሀገር መኖር ማለት ነው - እንደ ንጉሥ፤ እንደ መሪ (ፕሬዚዳንት፤ ጠ/ሚኒስትር ወዘተ) እንደ መንግሥት። በንጉሥ (በመንግሥት) የሚተዳደረው ህዝብ ልቅሶ፤ ሀዘን፤ ጉስቁልና፤ ድህነት ወዘተርፈዎች ሁሉ የንጉሡ (የመንግሥቱ) ልቅሶ ጉስቁልና፤ ድህነት ሊሆኑ ይገባል ማለቱ ነው - አርስጣጣሊስ። ንጉሡ (መንግሥት) የሚያደራጀው/ያደራጀው ሠራዊት ለገንዘብ የሚገዙ (ደሞዝተኞች) ለጦርነት የሚታዘዙ (በንጉሡ/በመንግሥት) ናቸው፤ ይህ ገንዘብ ከየት ይመጣል? በዘመናዊው መንግሥታዊ አጠራር ‘ታክስ’ ወይም ‘ግብር’ የሚባለውን ነው አርስጣጣሊስ ከመንጋው (ከህዝብ) የሚሰበሰብ ሀብት ነው ያለው።

ይህ ሠራዊት በንጉሡ (በመንግሥት) ስር የሚተዳደረውን ህዝብ የሚፈጅ፤ የሚያሰቃይ፤ የሚያሳድድ ሳይሆን የሚጠብቃቸው ሊሆን ይገባል ሲል ነው ንጉሥ እስከንድርን የመከረው። መንጋዎችም (ህዝብ) ቅንነት የሚገዛቸው ባሮች (በዘመኑ አጠራር የሀገሬው ህዝብ) ናቸው ማለቱ - በቅንነት እንጂ በሀይል በግፍ የምትገዛቸው ከሆነ የመንግሥትህ ፍፃሜ አያምርም ማለቱ ነው።

አገር የሚለማው ህዝብ የሚበለፅገው ቅን ፍርድ በመፍረድ ነው፤ አለው። ምን ማለቱ ነው? ሀገር የሚለማው ከህዝብ ጋር እንጂ ህዝብን አደህይተህ፤ ህዝብን በታክስ (በግብር) አራቁተህ ወይም ለድህነቱ መንስኤ ወይም መባባስ ምክንያቱ መሰረቱ (ንጉሡ/መሪው/ መንግሥቱ) ሆነህ - ሀገር አይለማም ማለቱ ነው፤ ፈላስፋው አርስጣጣሊስ። ሀገርና ህዝብ የሚበለፅጉት ተያይዘው፤ ተደጋግፈው ተቆራኝተው እንጂ ተገነጣጥለው ተጣጥለው፤ ተለያይተው አንዱ በሌላው አናት ላይ ቆመው አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም ማለቱ ነው አርስጣጣሊስ። መንገድ ብትቀድ፤ ህንፃ ብታቆም፤ ሆቴል ብታስፋፋ…ከህዝብ ጋር ካልሆነ መንገዱም ባዶ፤ ህንፃውም ቀፎ፤ ሆቴሉም ድረቅ ይሆናል ማለቱ ነው፤ ሲተረጎም።

ፍትህ (ቅን ፍርድ) ህዝብንና ህዝብን ያፋቅራል፤ ህዝብንና መንግሥትን ያስማማል - ሲል አርስጣጣሊስ ምን ማለቱ ነበር? እንደ መንግሥት ወይም እንደ ንጉሥ (እንደ መሪ) በመንግሥትህ ውስጥ የሚኖረውን ህዝብ በፍትህ (በቅን ፍርድ) በፍቅርና እና በእኩልነት ካላስተዳደርከው - በዘር፤ በሃይማኖት፤ በጉቦ፤ በዘመድ ወዘተርፈ ከከፋፈልከው ካመሰቃቀልከው በመንግሥትህ ውስጥ (በምታስተዳድረው ህዝብ) ፍቅርን ሳይሆን ፀብን ታመጣለህ ማለቱ ነው። እንዲህ ሲሆንም ፍቅር ያጣ ህዝብ፤ ፍትህ ያጣ ህዝብ፤ ከመንግሥቱ ጋር ስምምነት አይኖረውም ማለቱ ነው። መንግሥትና ህዝብ ካልተስማማ አመፅ፤ ጦርነት፤ ዕልቂት ይከተላልና ተጠንቀቅ ማለቱ ነው አርስጣጣሊስ ታላቁ እስከንድርን ሲመክር።

አርስጣጣሊስ በምክሩ መቋጫ፤ ዓለም ፀንቶ የሚኖረው ቅን ፍርድ በመፍረድ ነው፤ ማለቱስ እንደምን ይተረጎማል? ሠላም ፍቅር አንድነት በህዝብና በመንግሥት፤ በህዝብና በህዝብ መካከል የሚኖረው ፍትህ የሠፈነበት ሥርዐት፤ በፍትህ የሚያስተዳድር መንግሥት/ንጉሥ ሲኖር፤ አድልዖና ፍርደ ገምድልነት የሌለበት ቅን ፍርድ ለህዝብ የሚፈርድ መንግሥት/ንጉሥ/መሪ ሲኖር ብቻ ነው ማለቱ ነው ፈላስፋው። ቅንነት የሌለው አስተዳደር/መንግሥት በህዝብና በህዝብ መካከል፤ በመንግሥትና በህዝብ መካከል፤ በመንግሥትና በመንግሥት መካከል የዐመፅና የዕልቂት አዋላጅ ነው ማለቱ ነው አርስጣጣሊስ።

እነሆ ደግሞ ለአርስጣጣሊስ ማጠናከሪያ የሰጠውን ፈላስፋ እናቀርባለን፤

"ከፈላስፎች አንዱ እንዲህ አለ፤ ወገኖቹን በፍቅር የገዛ አፍአዊ ሰውነታቸውን ብቻ የገዛ አይደለም። ውስጣዊ ልባቸውንም ጭምር የገዛ እንጂ። ወገኖቹን በማስገደድ የገዛ ግን በከንቱ ይደክማል፤ በከንቱ ይለፋል።"

ይህ ፈላስፋ እቅጩን ዱብ አድርጓል። ህዝብን/ወገኖቹን በማስገደድ፤ በሀይል፤ በጠመንጃ፤ በአፈና፤ በስለላ፤ በእስር፤ በዛቻ . . . የሚገዛ በከንቱ ይደክማል - ስለምን? የህዝብ ፍቅር የለውምና አንድ ቀን ይወድቃል፤ አወዳደቁም ያስከፋል - ማለቱ ነው ፈላስፋዊ ባልሆነ ዕለታዊ የህይወት ቋንቋ ስንተረጉመው።

ደግሞም ስሙ ካልተገለፀ ፈላስፋ የሚከተለውን ነቅሰናል፤ "በክፉ ሰዎች መሾም ደጋጉን ሰዎች መከራ ያገኛቸዋል። በዐመፀኞች ሰዎች መንገሥ ደጋጉን ሰዎች የሥጋ ጉዳት ያገኛቸዋል። ወራዳ ባለጌዎች በሠለጠኑ ጊዜ ተስፋን ያስቀርጣሉ። ከመከራው ሁሉ የክፉ ሰዎች መሾም ይከፋል" ብሏል።

አንጋረ ፈላስፋውን እኛ ደግሞ ገፋ እናድርገው። ሀገር/መንግሥት በክፉ ሹመኞች፤ መሪዎች፤ አስተዳዳሪዎች እጅ የወደቀች እንደሆን ወዮ! ለህዝቡ ማለቱ ነው። እንዴት ቢሉ፤ ወራዳ ባለጌዎች በሠለጠኑ ጊዜ ህዝብን ሀገርን ተስፋ ያስቀርጣሉና - ይላል ፈላስፋው። ወራዳና ባለጌ ማለቱ በትምህርት ያልታነፁ፤ በሥነ ምግባር የተበላሹ፤ በትዕቢት የታጀሉ፤ ከራስ በላይ ነፋስ ያሉ፤ ከአንደበታቸው ያልታረሙ፤ ከእጃቸው ያልተሰበሰቡ እንዲህ ያሉ ሠዎች መንግሥት ሲሆኑ ህዝብን ተስፋ ያሳጡታል ማለቱ ነው ፈላስፋው። ተስፋ የቆረጠ ህዝብ ምን ይሆናል? ሀገር ሠላም ያጣል፤ ህዝብ ይታመሳል፤ ሰቆቃ ይበረታል፤ መተማማን ከቀዬ ይሰደዳል፤ ዐመፅ ይበረከታል። ክፉ ሠዎች መንግሥት ሆነው ሀገር ሲመሩ ህዝብን ራሱንም ሀገሩንም እስከ መጥፋት ያደርሱታል - ማለቱ ነው ፈላስፋው። ይህንን ትርጓሜ የሚያስረግጠውም - ከመከራ ሁሉ የክፉ ሠዎች መሾም ይከፋል፤ ብሏልና ፈላስፋው።

የክፉ ሰዎች ሹመት ደጋጎቹን ሰዎች ለሥጋ ጉዳት ይዳርጋቸዋል ማለቱስ? ክፉዎች መንግሥት ሲሆኑ ጥበበኞችን ምሁራንን ፀሀፍትን በጎ እና ቅን አሳቢዎችን የህዝብ ተቆርቋሪዎችን መከራና ፍዳ ውስጥ ይከቷቸዋል ማለቱ ነው። እንዲህ ያሉ የሀገር ተስፋዎች መካሪዎችና ቅን ሰዎች ለእስር፤ ለፍዳ፤ ለረሀብ፤ ለሥራ አጥነት፤ ለስደት በክፉ ሰዎች መንግሥት መሆን ምክንያት ይዳረጋሉ ማለቱ ነው - የሥጋ ጉዳት ይደርስባቸዋል ሲል። የእነዚህን ሰዎች ሥጋቸውን እንጂ ክፉ ሰዎች የሚያሸንፉት ህሊናቸውን አይደለምና።

እንግዲህ ደግሞ ቀጣዮቹን ፈላስፎች እናቀርባለን፤ "አፍላጦን የአህጉሮች ደህንነት በምን ይታወቃል? ቢሉት፤ ዐዋቂዎቻቸው ቢነግሡና ነገሥታቶቻቸውም ቢጠበቡ (ብልሆች አስተዋዮች) ቢሆኑ ነዋ ሲል መለሰላቸው።"

"ሶቅራጥስ ብልህ ዐዋቂ የሚባለው በማስተዋል የሚገዛና ምኞቱን የሚያሸንፍ ነው አለ። ደግሞም ንጉሥ ህዝቡን በቅንነት ከጠበቀና ከአስተዳደረ ጀግንነትና አሸናፊነት አያስፈልጉትም ብሏል።"

አጃኢበኛ የሆኑ ፈላስፎች። በኛ በኩል ማስፋፋት ከመጀመራችን በፊት ይህንን ለግንዛቤ እናቀርባለን። ቀደምቶቹ አፍላጦን ብለው የሰየሙት ፈላስፋ ፕሌቶ በመባል የሚታወቀውን ግሪካዊ ነው። እሱም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ428/427 ተወልዶ በ348/347 ከክርስቶስ ልደት በፊት አርፏል። ፕሌቶ በዐረብኛ ፅሁፎች ውስጥ አፍላጦን ተብሎ ይረጠራል/ይታወቃል። ግሪካዊው ፈላስፋ ሶቅራጥስ ትርጉማዊ ስሙም ያልተለወጠ ሲሆን የኖረውም ከክርስቶስ ልደት በፊት ሆኖ የተወለደበት ዘመን አልተመዘገበም። ህልፈቱ ግን በ399 ዓመተ ዓለም ነው። እንግዲህስ አነጋገራቸውን ጥቂት ብናራምደውስ?

የሀገር አልፎም የአለም ደህንነት በመንግሥት ወይም በመንግሥታት መሪዎች አስተዋይነት ይወሰናል ይላል ፈላስፋው አፍላጦን። ትዕቢተኞች ሥልጣን ሲይዙ ሠላም ትሰደዳለች ማለቱ ነው። ሀገር በጥጋበኞችና በደንቆሮዎች ስትመራ መዝሙሯ ሁሉ የሽብር፤ ከበሮዋ ሁሉ የዕልቂት አቀንቃኝ ይሆናሉ ማለቱ ነው አፍላጦን። ቋንቋቸውም ያዘው፤ እሰረው፤ ግደለው፤ አሳደው፤ ዝረፈው፤ ንጠቀው፤ ይሆናል ማለቱ ነው አፍላጦን። በሀገር ላይ ክፉ ዘመን የሚንሰራፋው ጥበብና ማስተዋል የሌላቸው ክፉ ሠዎች ሀገር ሲገዙ ነው ማለቱ ነው አፍላጦን።

እነሆ ሶቅራጥስም ይስማማል። በማስተዋል የሚገዛና ምኞቱን የሚያሸንፍ መሪ/ መንግሥት ብልህ፤ አዋቂ ይባላል ይላልና። ይህንን ስንበትነው የሚከተለውን እናገኛለን። ምኞቱን የሚያሸንፍ መሪ/መንግሥት ማለት ሥልጣን ሲይዝ፤ ሀገር ሲመራ፤ የሀገሩን ሀብት ለግሉና ለቤተሰቡ የማያጋብስ፤ ያማረውን ያሰኘውን የፈለገውን ሁሉ ያለማስተዋልና ያለዕቅድ ብድግ እያለ የማያደርግ ወይም የማይወስን፤ በመሰለኝና በደሳለኝ ፍርድ የማይሰጥ፤ ህግን የማይጠመዝዝና ህግን የራሱ ያማያደርግ፤ ጉቦ የማይበላ ለዘመድ አዝማድ የማያደላ ማለቱ ነው ሶቅራጥስ። በርሱ መንግሥት ሥር ለሚተዳደረው ህዝብ ሁሉ እኩል የሚፈርድ፤ የማያበላልጥ፤ የሁሉም

እረኛ ጠባቂ መሆኑን ተግብሮ የሚያሳይ ማለቱ ነው - ህዝብን በማስተዋል የሚገዛ ንጉሥ/መሪ - ብሎ ሲናገር ሶቅራጥስ።

ብልህ ዐዋቂ ጥበበኛ የሚመራው መንግሥት ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለራሱ (ስለ መንግሥቱ) ጀግንነት፤ ሃያልነት፤ አሸናፊነት በየዓመቱ፤ በየስድስት ወሩ፤ በየሳምንቱ በሬዲዮ፤ በጋዜጣ በካምቦሎጀ ጡሩንባ አይነፋም፤ አያቅራራም፤ አይጨፍርም፤ አይፏልልም ማለቱ ነው ሶቅራጥስ። ደግሞስ ማን በማን ላይ ነው የጀግንነት ጥሩንባ የሚነፋው? ማለቱ ነው ፈላስፋው። አስተዋይ መንግሥት በሚመራው ህዝብ ላይ አይፎክርም ማለቱ ነው ፈላስፋው። ሶቅራጥስ አስተዋይና ቅን መንግሥት የሚመራውን ህዝብ ጀግና ነኝ እያለ አያስፈራራውም ማለቱ ነው። ንጉሥ ወይም መንግሥት ህዝቡን በቅንነት ከመራና ካስተዳደረ የጀግንነትና የአሸናፊነት ፉከራ አያስፈልገውም ማለቱ ነው። ቅን የሆነ መንግሥት፤ ፍትሃዊ የሆነ መንግሥት ህዝብን ስለማይፈራ ጀግንነቱንና አሸናፊነቱን እንደ ውዳሴ ማርያም እየደጋገመ ህዝብን አያሸብርበትም ማለቱ ነው። ፉከራና ቀረርቶ የሚያበዛ ዘወትር ጀግንነቱን እየተረከ በራሱ ፉከራ ራሱ የሚሰክር መንግሥት ግን ፈሪ ቅንነትና ፍትሃዊነት የጎደለው ራሱ ሽብርተኛ መንግሥት ነው ማለቱ ነው ሶቅራጥስ፤ ይኸው ነው ትርጉሙ!

አንባቢ ሆይ! የጀመርነውን ንዑስ ርዕስ በሚከተለው ቋጭተን ወደ ቀጣዩ ንዑስ ርዕስ እንዘልቃለን። ቀጥሎ በምንነቅሰው ስሙ ባልታወቀው ፈላስፋ አነጋገር ውስጥ በቅንፍ የምታነባቸው (እስካሁንም በተነቀሱት ውስጥ በቅንፍ ያየሃቸውንና ወደፊትም የሚገጥሙህን ጨምሮ) ሊቁ ሊቀመዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ በግልፅ ቋንቋ ያፍታታልህን ነውና በእኛ በኩል ቃልም ሳናክልበት እነሆ፤

"ንጉሥ ሆይ፤ ህይወትህ የአታክልትህን ቦታ በመኮትኮትና በመንከባከብ እንደሆን ዕወቅ። (መንግሥትህ የምትፀናው አገርህን በመጠበቅና ህዝብህን ቅንና ርህራሄ ባለው አገዛዝ በማስተዳደር እንደሆን ዕወቅ)። የአታክልትህ ቦታ የፈረሰች ፈፅማ የጠፋች እንደሆን (ሀገርህ ፀጥታና ሠላም ያጣች ህዝብህ የተጎዳ እንደሆን) መንግሥትህ ፈፅማ ትጠፋለች፤ እንደምትጠፋ ዕወቅ። እንኪያስ የአታክልቶችህን ህንፃ ለማነፅ (ህዝብህን ለማስተዳደር) በየወገናቸው፤ በየመልካቸውና በየገዳቸው ለማደራጀት ዕሙድ ሆነህ የነቃህ የተጋህ ሁን።"

<u>ሠይፍ እና መፅሀፍ</u>

"ከዮናናውያን (ግሪኮች) አንዱ እንዲህ አለ፡ ዓለም ሠዎች ሃይማኖት እሊህ 3ቱ በሁለት ነገሮች የተያያዙ ናቸው። ሁለት ነገሮች የተባሉት ሠይፍ እና መፅሀፍ ናቸው። ቢሆንም ሠይፍ ከመፅሀፍ በታች ነው። (መፅሀፍ ይበልጣል) መፃህፍት ያነፁትን ህንፃ የዘመን ብዛት አያፈርሰውም።"

እነሆ በቃኘው ዕምነት ይህ የዓለም ህይወት ዋልታና ማገር የሆነ ጥልቅ ሀሳብ ነው። እንግዲህ ሠይፍ ማለት ሃይል ነው። ጉልበት ነው። ጦር ነው። ሠይፍ ማለት ሠራዊት ነው። ወታደር ነው። ሠይፍ ማለት ማስገበር ነው። ሀገራዊ ሉዐላዊነት ሲገሰስ ሲጣስ ሠይፍ ይመከታል። ከባዕድ ገዢ ነፃ ያወጣል ወይም ያላቅቃል። ይህ ዕውነት ነው። ሠይፍ ግን ሀገር አይገነባም። ሠይፍ የመኖር ነፃነትን ሠላምን አያሰፍንም። ሃይማኖትን በሠይፍ ማፅናት አይቻልም። ህዝብን በሠይፍ የሚገዛ መንግሥት ፅናት አይኖረውም። በሠይፍ የተማመነ በሠይፍ ይጠፋልና። ሲጠፋም በመልካም አይታወስምና። ሠይፍ ሠይፍን ይወልዳል እንዲል።

ፈላስፋው መፅሀፍ ከሠይፍ በላይ ነው ብሏል። እንዴት ማለት? መፅሀፍ ዕውቀት ነው። ጥበብ ነው። ምርምር ነው። ሳይንስ ነው። ሀሳብ ነው። ጥበብ ዕውቀት ምርምር ሀሳብ እኒህ ሀገር ገንቢ ናቸው። ጥበብ ምርምር ዕውቀት ሀሳብ - ነፃነት እንጂ ሠይፍ አይገዛቸውም። ነፃነት እንጂ ሠይፍ አያለማቸውም። ነፃነት እንጂ ሠይፍ አያሳድጋቸውም። መፃፍ ማንበብ መመራመር ሀሳብን በነፃነት መግለፅ ሀሳብን በሃሳብ ማንሸራሸር መወያየት - ሁሉም የአእምሮ ነፃነት ግኝት ናቸው። የአእምሮ ጭማቂ ውጤት። አእምሮ ደግሞ በሠይፍ አይታዘዝም። በሠይፍ መመራመር መጠበብ ማሰብ አይቻልም፤ በነፃነት እንጂ። የአእምሮ ነፃነት ውጤቶች የሆኑት ጥበብ ዕውቀት ምርምር ፈላስፋው መፅሀፍ በሚል በሸበበው ውቅያኖሳዊ አገላለፅ ውስጥ ይጠቃለላሉ። መፃህፍት ጋዜጦች መፅሄቶች፤ ዛሬ ዘመን ደግሞ ብሎጎች ድረ ገፆች . . . እኒህ ሁሉ ጥልቅ ፍልስፍናን በተላበሰው የፈላስፋው አገላለፅ - መፃህፍት ያነፁትን የዘመን ብዛት አያፈርሰውም - በሚል ተከሽነዋል።

ፈላስፋው በጥልቅ ባህረ ሀሳቡ 'ሠይፍ ከመፅሀፍ በታች ነው' ይላል። በዘመናዊው ዓለም ህልውና ሲመነዘር፤ የአእምሮ ነፃነት (መፅሀፍ) በአምባገነንና አፋኝ መንግሥት (ሠይፍ) ሥር መውደቅ የለበትም ማለቱ ነው። እንዲህ ሲሆን፤ ሠይፍ በመፅሀፍ ላይ ሲነግሥ - ዕውቀት ጥበብ ሀሳብ ምርምር በድምር አጠራራቸው የአእምሮ ነፃነትና ውጤቶቹ ይሠየፋሉ፤ ይጋዛሉ፤ ይሰደዳሉ - ማለቱ ነው። አምባገነንና አፋኝ መንግሥት መፅሀፍ ይፈራል። በሠይፍ ግን ይመካል። ምክንያቱም መንግሥቱ በዕውቀት፤ በጥበብ፤ በምርምር፤ በራስ መተማመን፤ በአእምሮ ነፃነት ዕምነት ላይ አልታነፀምና አልቆመምና። እንዲህ ያሉ መንግሥታት በፈላስፋው

ዘመን ነበሩ፤ ዛሬም አሉ። ይዋል ይደር እንጂ በሠይፍ የቆሙ መንግሥታት በመፅሀፍ ሀይል ይንኮታኮታሉ - ይላል ፈላስፋው። ስለ መፅሀፍ ሲሉ፤ ስለ አእምሮ ነፃነት ሲሉ በሠይፍ የተሰየፉ፤ ሠይፍ ሲንኮታኮት በሠይፍ መቃብር ላይ ህያው ሆነው ይታወሳሉ ይዘከራሉ - ይላል ፈላስፋው። ስለ መፅሀፍ ሲሉ ስለ አእምሮ ነፃነት ሲሉ፤ የተጋዙ የታሰሩ የተወገሩ የተሰደዱ ፀሀፍት ምሁራን የነፃነት ጠበቆች . . . ሠይፍን ድል ነስተው ነፃ መሆናቸው የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው - ይላል ፈላስፋው።

አንባቢ ሆይ፤ እነሆ ደግሞ ቀጣዩን የፈላስፋ አነጋገር አስተውል፤ "ከፈላስፎች አንዱ እንዲህ አለ፤ በሀገር ላይ ሀጢያት የተደረገ፤ ክፋት የተገለጠ እንደሆነ ጥበብ ከሀገር ወጥታ ትሸሻለች። ጥበብ ከሀገር ወጥታ የተለየችና የሸሸች እንደሆነ ህግ ትዋረዳለች። ህግም የተዋረደችና የተናቀች እንደሆን የንጉሥ ግርማ (መታፈር፤ መፈራት) ይጠፋል። ልብሰ መንግሥቱ ይገፈፋል።"

እንግዲህ እንዲህ እንጠይቅ፤ ሀገር ላይ ሀጢያት ክፋት የሚያደርግ ማን ነው? ሀገርን የሚያከፋው ወይም መኖሪያ መደሰቻ ተስማሚ ሠላማዊ የሚያደርገው ሀገርን የሚያስተዳድረው መንግሥት ነው። ሀገር እንዴት ይተዳደራል ሲባልም - ህዝብና መንግሥት እንዴት ይኗኗራሉ? ማለት ነው። ህዝብና መንግሥት ካብ ለካብ ይተያያሉ ወይስ ልብ ለልብ? ሀገር በህግ ትገዛለች ወይስ ህግን መንግሥት ይገዛታል/ ያዛታል? ህግ በመንግሥት የተዋረደች የተረገጠች እንደሆን፤ መንግሥት ህግ ጥሶ ህገ ወጥ የሆነ እንደሆን፤ ህግ ህዝብን ሀገርን ከመጠበቅና ከመንከባከብ ተዋርዳ መንግሥትን መሪን የምትጠብቅ የምትንከባከብ እንደሆን - ያኔ ህግ ተዋረደች፤ ያኔ ህግ ሞተች፤ ያኔ ህግ ማቅ ለበሰች - ይላል ፈላስፋው። በህግ ላይ ሠይፍ አክሊሉን ደፋ ማለት ነው።

ህግ የምትሞተው ጥበብ ከሀገር ለቅቃ ስትሸሽ ነው ይላል ፈላስፋው። ጥበብም ከሀገር የምትሸሸው ሀገር ጠባቂው፤ ህዝብ አስተዳዳሪው መንግሥት ሀገር ሲበድል ሀገር ሲያስለቅስ፤ ክፋቱ ጥፋቱ ልቅሶው ዋይታው፤ እስር ስደቱ ረሀብ ድህነቱ አድልዖውና ግፉ - በሀገረ በህዝብ ላይ ሲሰፍን ነው። ፈላስፋው ይህንን ነው - በሀገር ላይ ሃጢያት የተደረገ ክፋት የተገለጠ እንደሆን - የሚለው።

የጥበብ መሰደድ ማለት - አስተዋዮች ዐዋቂዎች ጥበበኞች ፀሀፍት ሀገር አይመዝበር፤ ህዝብ አይበደል፤ ህዝብ አይናቅ፤ ህዝብ ከህዝብ አይበላለጥ፤ ህዝብ አይፈናቀል፤ ነፃነት ይኑር ሠላም ይስፈን. . . ስላሉ በመንግሥት ሲወነጀሉ፤ አሸባሪ ሲባሉ ተወንጅለውም ሲገረፉ በእስር ሲማቀቁ ከሀገር ተገፍተው ሲወጡ - ያኔ ጥበብም ተሰደደች ማለት ነው ይላል ፈላስፋው። ጥበብ ሀገር ጥላ ወንዝ ተሻግራ የምትሰደደው ህግ የማያከብር ጡንቻውን የተማመነ ሠይፍ ብቻ የሚያወዛውዝ ግብዝ መንግሥት ሀገር ሲያስተዳድር ሀገር ሲመራ ነው - ማለቱ ነው ፈላስፋው። እንዲህ ያለ መንግሥት ክብሩን የተገፈፈ ከነ ሀፍረቱ የቆመ መንግሥት ነው - ማለቱ ነው ፈላስፋው። ምክንያቱም ይህ መንግሥት በእኩዮች፤ በደናቁርት፤ በትዕቢተኞች በክፉ ሠዎች እጅ የወደቀ መንግሥት ነውና እርቃኑን ሆኗል ማለት ነው ይላል - ፈላስፋው። ፈላስፋው - ህግም የተዋረደችና የተናቀች እንደሆን የንጉሡ ግርማ (መታፈር፤ መፈራት) ይጠፋል። ልብሰ መንግሥቱ ይገፈፋል - ማለቱ ይኸው ነው ትርጉሙ!

እነሆ በእኛ በኩል ወደ ማደሪያችን ማዝገሚያ ሰአታችን ደረሰ። እና ከማሳረጋችን በፊት ያለተጓዳኝ ማብራሪያ እንደወረደ የሚከተለውን ነቅሰናልና አስቀድሞ ከወረደው ምልከታ ጋር አጣጥመው፤

"ሁለት ቀንዶች ባሉት በንጉሥ እስክንድር ፊት ፈላስፎች ይህን ተናገሩ። ማነንን የማይፈራውን ማንም አይፈራውም። ከዐመፅ ርቆ ቅን ፍርድ ፈርዶ ፍርዱ ያልፀናለት፤ ቅን መፍረዱና ከዐመፅ መራቁ ያልረዳው ማን ነው። ቅን ፍርድ ለሚፈርድ ፍጥረቱ ሁሉ ይታዘዝለታል። ሳያዝን ሳይተክዝ ይኖራል። አጃቢ ሠራዊት አያሻውም። የሠዎቹን ልብ ሁሉ ማርኮታልና ጠላት አለብኝ ብሎ አይፈራም። እርሱ ያዘዘውን ትዕዛዝ የሚተላለፍ የለም። ቅን ፍርድ መፍረዱን የሚያውቁለትና ቅን የፈረደላቸው ሁሉ ጭፍሮቹ ይሆኑለታል።"

<u>ማሳረጊያ</u>

ክብርና ምሥጋና አንጋረ ፈላስፋን ከላቲንና ከዐረብኛ ወደ ግዕዝ ለመለሱት ቀደምት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አባቶቻችን ይሁንና፤ ክብርና ምሥጋና አንጋረ ፈላስፋን ከግዕዝ ወደ አማርኛ ለመለሰው የታላላቆቻችን ታላቅ ትውልድ አካል ለሆነው ሊቁ ሊቀመዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ይሁንና፤ እነሆ የፈላስፎችንና የዐዋቂዎችን ምሥጢረ ጥበብ ከታላቁ ቅዱስ መፅሐፍ ጋር አዛምዶ የተረጎመልንን በእኛ በኩል እንዳቅማችንና እንደዘመናችን ቃኘተን አበቃን። እንግዲህ በጎደለ ሙላበት። በጎበጠ አቃናበት።

አንጋረ ፈላስፋንና ህልቆ መሳፍርት የሆኑና ገና ገሀድ ያልወጡ (ለትውልድ ዕይታ፤ ለንባብ ያልበቁ) የታሪክ፤ የምርምር፤ የፍልስፍና እና የዕምነት የግዕዝ መፃህፍትን በየገዳማቱ፤ በየአድባራቱና በየጥንታውያን አብያተ

ክርስቲያናት ከጥፋት ከዘረፋና ከውድመት በሠማዕትነት ጭምር ጠብቃ ላኖረችው ቅድስት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሄር አብ ሠላም ቸርነትና ፍቅር ዛሬም ነገም እስከ ወዲያኛውም ከእርሷ ጋር ይሁን፤ ዓሜን! ታሪክንና ቅርስን ጠብቀው ለትውልድ ላቆዩልን የቤተክርስቲያኗ ሠማዕታትም የክርስቶስ ፍቅርና ፀጋው ዘወትር አይለያቸው።

ቃኚው እንዲህ ይጠይቃል፤ በገዳማት፤ በዋሻዎችና በአስቸጋሪ ቦታዎች ጭምር (ከጥፋት ለመከላከል እንደሆን ይታወቃል) በተተከሉት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አባቶች ሊቃውንት እግዚአብሄርን ከማገልገል ጋር በብቸኝነትና በብህትውና ሲኖሩ ዘመናቸውን የገፉት መፃህፍትን በመመርመር፤ በማጥናት፤ በመተርጎምና በመፃፍ ነበርን? ስለራሳቸው የማይናገሩት ሊቃውንት አባቶች ኢትዮጵያውያን (አንጋረ ፈላስፋን የተረጎሙት ስማቸው እንኳ የለም) በተረጎሙትና ሊቁ ሊቀመዘምራን ሞገስ ለእኛ ባስተላለፉልን የፈላስፎች አነጋገር ትርጉም ውስጥ ልብ ብሎ ለተመለከተው ሥራቸውንና ዘመናቸውን የሚያሳብቅ ምላሽ ያገኛል። እንዲህ ተፅፏልና፤

"በተባህትዎ የሚኖር አንዱን ፈላስፋ በብቸኝነት መኖርን እንዴት አደርገህ ትታገሰዋለህ? ቢሉት እንዲህ አለ። እኔ'ኮ ብቻዬን የምኖር አይደለሁም። ከሚመክሩኝና ከሚገስፁኝ፤ ከሚያጫውቱኝና የሚያወያዩኝ ከብዙ ሠዎች ጋር ነው ያለሁ። ጨዋታን ከፈለግሁ ከእነሱ ጋር እጫወታለሁ። ወግ ሲያምረኝ ከእነሱ ጋር አወጋለሁ። መወያየት ሲያስፈልገኝ ከእነሱ ጋር እወያያለሁ። እነሱ ያጫውቱኛል፤ ያወያዩኛል ብሎ እጁን ዘርግቶ ከጎድኑ መፃህፍትን አወጣና፤ ይህ አብሮኝ የሚኖረውና የሚያወያየኝ ጋሊኖስ ነው። ይህም የሚመክረኝ አብቅራጥ ነው። ይህ የሚገስፀኝ ዲዮጋንስ ነው። ይህ በጎ በጎውን እያመጣ የሚያጫውተኝ አፍላጦን ነው። አርስጣጣሊስ ይመሰክራል። ሕርሙስ ያጫውታል። ዳዊት ይዘምራል። ሠለሞን ይገስፃል። ሲራክ ይመክራል። ባስሊዮስ ያስተምራል። ጎርጎሪዮስ ይናገራል። ሐዋርያ ይሰብካል። ወንጌል ያበሥራል። ከነዚህ ሁሉ ከፈቀድኩት ጋር እናገራለሁ፤ እጫወታለሁ፤ እወያያለሁ፤ እሱም ከኔ ጋር ይጫወታል። የተዘነጋኝን ነገር ያስታውሱኛል። በተባህትዎ (በብቸኝነት) ጉዳዩን ፈፅሞ ጥርጥር አይገባኝም አለ።"

ቃኚው ደግሞ ለራሱ ይህንን ይላል፤ ነፍሴ ሆይ ስለምን በቀደመው ዘመን ተፈጥረሽ ከቀደሙት ጋር አልኖርሽም?!

------------------------/// ተ ፈ ፀ መ ///--------------------------

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይታደጋት!
ለመልዕክት፤ mmtessema@gmail.com